# ADDA BILISUMMAA OROMOO

**OROMO LIBERATION FRONT**

**جبهة تحرير اورومو**

Gaafa: 20/07/2015
Date: تاريخ

Lakk.: 13/stm - abo/2015
No.: رقم

## የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ወታደራዊ መግለጫ

**የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት በምስራቅ ኦሮሚያ በፈዲስ ወረዳ ከሐረር ከተማ 20ኪሜ ርቆ በሚገኝ ቦባሳ በተባለ ቦታ በጠላት ወታደራዊ ካምፕ ላይ በወሰደው ወታደራዊ እርምጃ ከ28 በላይ የጠላት ወታደሮችን ከጥቅም ውጪ ኣደረገ።**

ጀግናው የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት የኦሮሞ ህዝብን ነጻነትና የኦሮሚያን ሉዓላዊነት ለማረጋገጥ በጠላት ላይ የሚወስደውን እርምጃ በማጠናከር ሰሞኑን በምስራቅ ኦሮሚያ በወሰደው ኣኩሪ እርምጃ ኣንጸባራቂ ድል ኣስመዝግቧል።

በዚሁ መሰረት በምስራቅ ኦሮሚያ ውስጥ የሚንቀሳቀሰው የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ሃምሌ 16 ቀን 2015ዓም ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ፈዲስ ወረዳ ቦኮ ኣካባቢ ቦባሳ በተባለ ቦታ የሚገኘውን የወያኔ ጦር ካምፕ በመውረር በወሰደው ጥቃት ከ28 በላይ የጠላት ወታደሮችን ከጥቅም ውጪ ኣድርጎ የጦር መሳሪያ ጨምሮ በርካታ ቁሳቁሶችን በመማረክ ለኦሮሞ ህዝብ የነጻነት ትግል እንዲውል ማድረጉን የምስራቅ ኦሮሚያ ዞን የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ዕዝ ኣስታውቋል።

ጀግናው የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት በዚሁ ጥቃት 13 የወያኔ ወታደሮችን ገድሎ ከ15 በላይ ማቁሰሉን የገለጸው የዞኑ የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ዕዝ ከዚህም ሌላ 17 AK-47 ጠብመንጃዎች፥ ከ4000 በላይ ልዩልዩ ጥይቶች፥ 23 የእጅ ቦምቦች፥ 27 ወታደራዊ ትጥቆች፥ 2 ኣይኮም ( *ICOM*) የተባሉ የመገናኛ ራዲዮዎች፥ 6 የሞባይል ስልኮች እንዲሁም የስንቅ ማከማቻን በመቆጣጠር የተለያዩ ቁሳቁሶችን በመማረክ ለነጻነት ትግሉ ማዋሉን ገልጿል።

የምስራቅ ዞን የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ግንቦት 16 ቀን 2015ዓም በኦቦራ መልካ-በልአ ወረዳ ጀሎ በተባለ ቦታ በኣካባቢው ህዝቡን ሲያንገላታ የነበረውን ሁሴን ኣህመድ ሙሳ የተባለ የወያኔ የደህንነት ሹም በወሰደበት የማያዳግም እርምጃ መግደሉና፡ ግንቦት 23 ቀን 2015ዓም ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ጨለንቆ ወረዳ ገንደ-ጎዲ በተባለ ቀበሌ ውስጥ ደግሞ ሙሐመድ ኣብራሂምና ኡመር ሲዮ የተባሉ የወያኔ ፖሊሶችን በቁጥጥሩ ስር ማዋሉ ይታወሳል። ከዚህም ሌላ ግንቦት 24 ቀን 2015ዓም የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ልዩ ሃይል በምስራቅ ኦሮሚያ ዞን ሐረር ከተማ ኣቅራቢያ ሁንደኔ በተባለ ቦታ በኣካባቢው የፖሊስ ኣዛዥ በመሆን ህዝቡን ሲያንገላታ በነበረው የጠላት ቅጥረኛ 50ኣለቃ(ሳጅን) ኣበበ ኣሰፋ ላይ የማያዳግም እርምጃ ወስዷል። በዚሁ ዕለት በሃረማያ ወረዳ ፊንቂሌ ተብሎ በሚጠራ ቀበሌ ውስጥ በምርጫ ስም ነዋሪውን ሲያዋክቡ የነበሩ የወይኔ ፖሊሶችን በማጥቃት 4ቱን ማቁሰሉ ይታወሳል።

ከዚህም ሌላ በደቡብ ኦሮሚያ የሚንቀሳቀሰው የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ግንቦት 30 ቀን 2015ዓም በቦረና ዞን ሞየሌ ከተማ ቀበሌ 02 ውስጥ የሚገኘውን የወያኔ ጦር የሰፈረበትን የጉምሩክ ግቢ በማጥቃት 12 ወታደሮችን ገድሎ ከ15 በላይ ኣቁስሏል። የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ጥቃቱን ኣጠናክሮ በመቀጠል ሃምሌ 6 ቀን 2015ዓም እዚያው ቦረና ዞን ሚኦ ወረዳ ሜጢ ቀበሌ ውስጥ ሰፍሮ የሚገኘውን የወይኔ ጦር በማጥቃት 3ቱን ገድሎ ከ4 በላይ ማቁሰሉ ይታወሳል።

በጠብመንጃ ኣፈሙዝ የኦሮሞ ህዝብን ለጭቆና ዳርጎ ነጻነቱንና የሃገር ባለቤትነት መብቱን ነፍጎ ለከፋ የሙብት ረገጣ እየዳረገ ያለውን ኣምባገነናዊ የወያኔን ስርዓት በማስወገድ የኦሮሞን ህዝብ ነጻነትና የኦሮሚያን ሉዓላዊነት ለማረጋገጥ እያደረገ ያለውን ፍልሚያ ይበልጥ ኣጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት በድጋሚ ያረጋግጣል።

ድል ለኦሮሞ ህዝብ!

የኦሮሞ ነጻነት ግንባር

ሃምሌ 20, 2015ዓም

P.O. Box 6973 Asmara, Eritrea Tel 2911 110236 Email: Caalchis@gmail.com, *www.oromoliberationfront.org*